# የአሽከርካሪ እና ተሽከርካሪ ደህንነት

Standard

**ይዘቶች**


1 **መግቢያ** ... 3

2 **መማሟላት የሚገቡ ነገሮች** ... 3

3 **የአሽከርካሪ አስተዳደር** ... 4

3.1 ሞተር ብስክሌቶች ... 4

3.2 ከፍተኛ የአደጋ ተጋላጭነት ያላቸውን አሽከርካሪዎች ስለ መቆጣጠር ... 4

3.3 ተሽከርካሪ መሰረት ያደረጉ የሬዲዮ ሽፋን የዳሰሳ ጥናቶች ... 4

3.4 የማሽከርከር ብቃትን ሊያስተጓጉሉ የሚችሉ ምክንያቶችን መቆጣጠር ... 5

3.5 በተሽከርካሪ መሳሪያዎች ... 5

3.6 በተሽከርካሪ እንቅስቃሴ ... 5

3.7 ስልጠና ... 5

3.7.1 የተጋቦት ስልጠና ... 5

3.7.2 የአሽከርካሪ ንቃት ስልጠና ... 5

3.7.3 የማሻሻያ ስልጠና ... 6

4 **ክትትል እና ግምገማ** ... 6

5 **የለውጥ መረጃ** ... 6



© Ericsson AB 2024

ሁሉም መብቶች የተጠበቁ ናቸው። በዚህ ሰነድ ውስጥ ያለው መረጃ የኤሪክሰን ንብረት ነው እና ያለ ማስታወቂያ ሊለወጥ ይችላል። ኤሪክሰን ለእውነት ስህተቶች ወይም የጽሁፍ ስህተቶች ምንም አይነት ሃላፊነት አይወስድም።

## 1 መግቢያ

ይህ መስፈርት በኤሪክሰን የንግድ ተቋም ቦታ ላይ ሲነዱ የጤና እና የደህንነት ሁኔታዎች በስርዓት መስተዳደራቸው የሚያረጋግጡ በትንሹ ማሟላት የሚያስፈልጉ ነገሮችን ይገልጻል።

## 2 መማሟላት የሚገቡ ነገሮች

የሚከተሉ መማሟላት የሚገቡ ነገሮች የሚተገበሩ ይሆናል፡

- በእጅ የሚያዙ ስልኮችን እየነዱ መቼም አይጠቀሙ። ይህም አጭር የጽሁፍ መልእክት፣ የቪድዮ ጥሪ እና ድምጽንም ያካትታል ግን በዚህ ብቻ አይገደብም። ለድምጽ ብሉቱዝ ወይም ተመሳሳይ አይነት መገናኛ መጠቀም ይቻላል። ጥሪው የአደጋ ጊዜ ከሆነ - ደህንነቱ በተረጋገጠ ቦታ ያቁሙና ጥሪውን ይውሰዱ።

- ሁሉም ተሽከርካሪዎች (1> እንደ ፍሬን፣ የመሪ ጥርሶች፣ ጥሩምባ፣ የተሽከራካሪ መስታዎት ዝናብ መጥረጊያዎች፣ የኋላ መስታወቶች እና መብራቶች ያሉትን ወሳኝ አካሎች ጨምሮ በአምራቾች ደንቦች መሰረት የተጠበቁ መሆናቸውን እና ተቀባይነት ያለው አገር አቀፍ የድህንነት ምርመራ ሰርተፍኬት ያላቸው መሆኑን ያረጋግጡ።

- የታርጋ ቁጥር፣ የተሽከርካሪ የታርጋ ቁጥር፣ የሞተር ተሽከርካሪ የምዝገባ ሰርተፊኬት እና የተሽከርካሪው መደበኛ የምርመራ ሰርተፍኬት ያረጋግጡ።

- ከአምራቹ ከፍተኛ የተወሰነ ክብደት በላይ ተሽከርካሪው ላይ መቼም አይጫኑ።

- በአሽከርካሪው እና ሁሉም በጥቅም ላይ የዋሉ የተጓዥ መቀመጫዎች የጭንቅላት ማሳረፊያ የሚገጠምላቸው ይሆናል።

- አሽከርካሪው እና ሁሉም ተሳፋሪዎች የደህንነት ቀበቶ ማሰር አለባቸው።

- መቼም ለመንገዱ አይነት፣ ተሽከርካሪ ወይም ሁኔታ አደገኛ በሚሆን ፍጥነት አይጓዙ ወይም የፍጥነት ገደቦችን አይለፉ።

- መቼም ማሽከርከር ላይ ተፅኖ ያለው ድካም ወይም የህክምና ሁኔታ ካለ  አያሽከርክሩ።

- ግደባዎች የሚመለከታቸው የህክምና እጾችንም ጨምሮ በአልኮል ወይም በእጽ ተጽኖ ስር ሆነው መቼም አያሽከርክሩ።

- ከሁለት ሰዓታት በላይ ሲነዱ እንደ አስፈላጊነቱ ለእረፍት ጊዜያት ያቁሙ።

- ከሶስት ሰዓታት በላይ መንዳት ለሚያስከትል የትኛውንም አይነት እንቅስቃሴ ሲያቅዱ ከመንዳት ጋር የተያያዙ ሁሉም አደጎች የተመናመኑ እንደሆኑ ለማረጋገጥ የአደጋ ጊዜ ግምገማ ያካሂዱ።

- ለባለሙያ አሽከርካሪዎች የሃገር አቀፉን ህጋዊ የጊዜ ገደብ መቼም አይለፉ።

- የተበላሸ መኪና ጎትቶ መውሰድ ሁሌም ከሙያዊ አገልግሎት በሆነ የስበት መኪና መደረግ አለበት (የብረት ዘንጎች እና ሰንሰለቶች ሳይሆኑ)።

- የጉዞ ርዝመት፣ የጭነት ሁኔታ እና የአየር ንብረት ግምትን በማሰብ ደህንነቱ የተጠበቀውን ጉዞ ያቅዱ።

- አስፈላጊ የአሽከርካሪ ስልጠና መካሄዱን ያረጋግጡ።

- አሽከርካሪው በሁሉም ጊዜ ተቀባይነት ያለው የመንጃ ፍቃድ እና በጥቅም ላይ ለዋለው ተሽከርካሪ ዋስትና ሊኖረው ይገባል።

# 3 የአሽከርካሪ አስተዳደር

## 3.1 ሞተር ብስክሌቶች

ሞተር ብስክሌቶች እንደ የትራንስፖርት አማራጭ መገልገል ወይም እቃዎችን ለማድረስ መጠቀም አይፈቀድም።

## 3.2 ከፍተኛ የአደጋ ተጋላጭነት ያላቸውን አሽከርካሪዎች ስለ መቆጣጠር

እንደተዘረዘሩት እንቅስቃሴዎች ለተሽከርካሪ አደጋ ከፍተኛ ተጋላጭነት ያላቸው አሽከርካሪዎች ሊለዩ እና ተጨማሪ የአከባቢያዊ የአሽከርካሪ ስልጠና ሊተገበር ይገባል፡

- ከፍተኛ ርቀት ማሽከርከር።
- አደገኛ ሸቀጦችን በህዝብ መንገዶች ላይ ለማጓጓዝ ተሽከርካሪ መንዳት።
- ከመንገድ ውጭ ተሽከርካሪ መንዳት።

የትኛውም ግለሰብ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ትናንሽ አደጎች ካጋጠሙት ተጨማሪ አደጋዎችን ለመከላከልተጨማሪ አከባቢያዊ ስልጠና ሊሰጥ ይገባል ወይም ሌሎች ወሰኝ እርምጃች ሊወሰዱ ይገባል።

## 3.3 ተሽከርካሪ መሰረት ያደረጉ የሬዲዮ ሽፋን የዳሰሳ ጥናቶች

ለሬዲዮ ሽፋን የዳሰሳ ጥናቶች የእይታ ምስል ማሳያዎች ጥቅም ላይ ሲውሉ በተሽከርካሪው የፊተኛው በኩል ሊገጠሙ ይገባል እና አሽከርካሪውን ሃሳብ እንዳይሰርቁ ተደርገው ሊቀመጡ ይገባል። የምስል መሳያዎቹ ላፕቶፖች ላይ ለድህንነት ምክንያቶች ጥቅም ላይ እንደሚውሉት "ሁድ" ወይም የግላዊነት ማጣሪያ ሊገጠምላቸው ይገባል። አሽከርካሪው ተሽከርካሪው በእንቅስቃሴ ላይ ሳለ የዳሰሳ መሳሪያዎቹን ከመጠቀምም ሆነ ከማስተካከል ይታገዳል።

የሬድዮ ዳሰሳ ጥናት ተሽከርካሪዎች የእሳት ማጥፊያ እና የተመቻቸ የመጀመሪያ ኣርዳታ መስጫ ከረጢት ሊኖራቸው ይገባል።

## 3.4 የማሽከርከር ብቃትን ሊያስተጓጉሉ የሚችሉ ምክንያቶችን መቆጣጠር

ብዙ ምክንያቶች ትኩረትን ሊነኩ ይችላሉ እናም ይህንን በማድረግ የአደጋን ተጋላጭነት ሊጨምሩ ይችላሉ። በትንሹ የሚከተሉትን መከተል ይገባል።

## 3.5 በተሽከርካሪ መሳሪያዎች

ተሽከርካሪው በእንቅስቃሴ ላይ ሳለ የቢሮ መሳሪያ፣ የማስታውሻ ደብተሮች፣ የልዩ ልዩ መገናኛ መሳሪያዎች ወዘተ በአሽከርካሪው መቼም ጥቅም ላይ ሊውሉ አይገባም።

እንደ ሬድዮ፣ የአሰሳ ስርዓቶች (የመንገድ መመሪያ) እና መጨናነቅ የማስጠንቀቂያ ስርዓቶች በተሽከርካሪ ውስጥ ባሉ ስርዓቶች የአሽከርካሪው ሃሳብ መስረቅ አደጋ ካለ የትኞቹንም እንደዚህ ያሉ ስርዓቶች የአሽከርካሪውን ሃሳብ የሚሰርቁ ከሆኑ አሽከርካሪው ከማሰራት ወይም ከማስተካከል የታገደ ነው።

## 3.6 በተሽከርካሪ እንቅስቃሴ

ብሄራዊ ህግ በሌለበት አሽከርካሪው አይኑን ከመንገዱ ላይ እንዲያነሳ ወይም በአንድ እጅ ትርጉም ላላቸው ክፍለ ጊዜያት እንዲያሽከረክር ወይም የሃሳብ መሰረቅን የሚያስከትሉ ማንኛውም እንቅስቃሴዎች የተከለከሉ ናቸው።

ልብ ይበሉ አሽከርካሪው በሁሉም ጊዜያት ተሽከርካሪው ሙሉ ለሙሉ በቁጥጥሩ ስር መሆን እንዳለበት ።

## 3.7 ስልጠና

ቅድመ ግምገማ ለአዲስ መጤዎች እና አዲስ አሽከርካሪዎች አስገዳጅ መሆን አለባቸው። አሽከርካሪ ንቃት ስልጠና፣ ደህንነቱን የጠበቀ አነዳድ ስልጠና፣ የላቀ እና የመከላከያ አነዳድ ስልጠና እንደ ልዩ ስልጠናዎች በተጨማሪም ለማታ አሽከርካሪዎች የማታ አነዳድ ስልጠና እና ለጣቢያ ቡድኖች ከመንገድ ውጪ አንዳድ ይሰጣል።

### 3.7.1 የተጋቦት ስልጠና

የተጋቦት ስልጠና በማሽከርከር ላይ ስለ ሞባይል ስልኮች ሲጠቀሙ ያለውን አደጋዎች ያሳውቅል። በመስሪያ ቦታ አሽከርካሪ የሚቀርብላቸው ስልጠናው ግለሰቡ ከተሽከርካሪው እና መቆጣጠሪያዎቹ ጋር መተዋወቁን ስልጠናው ማረጋገጥ አለበት። እንደዚህ አይነት ስልጠና የሚካሄደው ግለሰቡ በመጀመሪያ የሚቀርብለት ተሽከርካሪ ጋር ከዚህ በፊት ምንም አይነት ልምድ ከሌለው ነው።

### 3.7.2 የአሽከርካሪ ንቃት ስልጠና

መንዳት የእነሱ ሚና ጉልህ አካል ለሆነላቸው ግለሰቦች ሁሉ መደበኛ የንቃት ስልጠና ይሰጣል። ኤሪክሰን ደህንነቱን የጠበቀ አነዳድ ንቃት ስልጠና ይሰጣል።

### 3.7.3 የማሻሻያ ስልጠና

በአደጋ መጠን ወይም በአካባቢያዊ ተጋላጭነት ግምገማ በኩል ሌሎች ተመሳሳይ ስራ ከሚሰሩ ከፍተኛ የጉዳት ተጋላጭት ለሚያሳዩ አሽከርካሪዎች የማሻሻያ ስልጠና  የሚቀርብላቸው ይሆናል። በማሻሻያ ስልጠና በኩል ለአብዛኞቹ አደጎች አስተዋፆ የሚያደርጉ ጉልህ ድክመቶች ሊለዩ እና ሊዳሰሱ ይገባል።

## 4 ክትትል እና ግምገማ

ለዚህ መስፈርት ተገዢነት ክትትል ሊደረግበት እና ሊገመገም ይገባል። ለሚከተሉት መዝገቦች ሊያዙ ይገባል፡

- ቅድመ ሁኔታ/የኤሪክሶን ተሽከርካሪ ወይም በኤሪክሰን ፋንታ ከመንዳት በፊት ሊጣሩ የሚገባ ነገሮች። ማጣራት፡ ህጋዊ የመንጃ ፍቃድ፣ የትራክ መዝገቦች (ያለፉ ቅጣቶች፣ አደጋዎች ወዘተ።)።
- የአጋጣሚ ስታትስቲኮች።
- የመድን ይገባኛል ጥያቄ ሪፖርቶች።
- የፍቃድ ማረጋገጫ እና የሁኔታ ለውጦች።
- ስልጠና።

## 5 የለውጥ መረጃ

ካለፈው ግምገማ ወዲህ የለውጦች አጭር መግለጫ፡

1. ሞተር ብስክሌቶች እንደ የትራንስፖርት አማራጭ መገልገል ወይም እቃዎችን ለማድረስ መጠቀም ላይ ክልከላን አስቀምጧል።